# ስለገለልተኛ የቅሬታ አፈታት ሂደት

የሚወክላቸውን ሌላ ሰው ካልቀጠሩ በስተቀር፣ ወላጆች ጉዳያቸው የሚሰማው ያለምንም ክፍያ ነው::

❧

በሚቻለው ሁኔታ ሁሉ ጉዳዩ እንዲሰማ የሚደረገው ለወላጆች በሚስማማ ጊዜና ቦታ ነው::

❧

ጉዳዩ የሚሰማው በሜሪላንድ የአስተዳደራዊ ጉዳዮች ሰሚ ቢሮ በሚቀጠር የአስተዳደራዊ ህግ ዳኛ ነው::

❧

እንግሊዝኛ የመጀመሪያ ቋንቋቸው ያልሆኑ ወላጆች አስተርጓሚ እንዲገኝላቸው ሊደረግ ይችላል፣ ወይም አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ልዩ አይነት የመገናኛ ዘዴ ሊመቻችላቸው ይችላል::

❧

ተጨማሪ ኢንፎርሜሽን ይፈልጋሉ? እንግዳውስ ቀጥሎ የተመለከቱት ማጣቀሻዎች ስለቅድመ-ጣልቃገብነት ዘዴ የወላጆች መብቶች የበለጠ ኢንፎርሜሽን ይሰጡዎታል::

- ❧ ክፍል(ሎች) 8-416, የሜሪላንድ ደንብ ማብራሪያ::
- ❧ COMAR 13A.13.01
- ❧ ሕዝባዊ ህግ 105-17፣ የአካል ጉድለት ያለባቸው ግለሰቦች ትምህርት ድንጋጌ ማሻሻያ ክፍል C
- ❧ ክፍል 303፣ የፌደራል ህግጋቶች ደንብ ርዕስ 34
- ❧ ክፍል 300፣ ንዑስ ክፍል 560-577፣ የፌደራል ህግጋቶች ደንብ ርዕስ 34
- ❧ ክፍል 99፣ ርዕስ የፌደራል ህግጋቶች ደንብ ርዕስ 34

**የነዚህን ሰነዶች ቅጂ ለማግኘት፣ ቀጥሎ በተመለከቱት አድራሻዎች ይጠይቁ፣**


የሜሪላንድ ክፍለ-ግዛት የትምህርት ክፍል
የልዩ ትምህርት ቅርንጫፍ/የፈጥኖ ጣልቃ ገብነት አገልግሎት፣
**Maryland Infants and Toddlers Program**
200 West Baltimore Street; Baltimore, MD 21201
(410) 767-0261 በድምጽ • (800)535-0182 ከክፍያ ነጻ የድምጽ
(410) 333-8165 ፋክስ • (410) 333-0731 TDD



Robert L. Ehrlich, Jr.
*ገዢ*

Edward L. Root
*ፕሬሲደንት፣ የሜሪላንድ ክፍለ-ግዛት የትምህርት ቦርድ*

Nancy S. Grasmick
*የክፍለ-ግዛቱ የትምህርት ቤቶች የበላይ ተቆጣጣሪ*

Carol Ann Baglin
*ረዳት የትምህርት ቤቶች የበላይ ተቆጣጣሪ*
*የልዩ ትምህርት ቅርንጫፍ/የፈጥኖ ጣልቃ ገብነት አገልግሎት*



የሜሪላንድ ክፍለ-ግዛት የትምህርት ክፍል፣ ለቅጥር ሥራም ሆነ ፕሮግራምን ለመጠቀም፣ በዘር፣ በቀለም፣ በጾታ፣ በእድሜ፣ በትውልድ ወይም ብሄር፣ በሃይማኖት፣ ወይም በአካለ-ጎደሎነት ላይ የተመሰረተ ልዩነት አያደግም:: የዲፓርትሜንቱን ፖሊሲ በተመለከተ ጠይቆ ለመረዳት፣ የዕኩልነት ዋስትና አስከባሪ ቅርንጫፍን በሚከተሉት አድራሻዎች ያነጋግሩ:: Equity Assurance and Compliance Branch 410-767-0246 በድምጽ 410-333-2226 ፋክስ ወይም 410-333-6442 TDD. ✦ ይህ ሰነድ ከዩናይትድ ስቴትስ የትምህርት ክፍል፣ የልዩ ትምህርት ክፍልና የማህበራዊ ባህሪያት ማረሚያ ቢሮ፣ IDEA፣ ክፍል C፣ እርዳታ #H181A020124. ✦ በተገኘ ገንዘብ፣ በልዩ ትምህርት ቅርንጫፍ/የፈጥኖ ጣልቃ ገብነት አገልግሎቶች ቅርንጫፍ አማካኝነት ተቀነባብሮ የታተመ ነው:: ✦ በዚህ ሰነድ ውስጥ የተገለጹት አመለካከቶች የግድ የዩናይትድ ስቴትስን የትምህርት ክፍል ወይም የማንኛውንም ሌላ የፌደራል ኤጀንሲን አመለካከት የሚያንጸባርቁ ላይሆኑ ይችላሉ፣ ስለሆነም በዚህ መልኩ መታየት የለባቸውም:: ኢንፎርሜሽኑ ከህትመት ባለቤትነት የመብት ገደብ (ኮፒ ራይት ነጻ) ነው:: አንባቢዎች ቅጂውን እያባዙ እንዲያዳርሱና እንዲያስነብቡት ይበረታታሉ፣ ነገር ግን፣ እባከዎ ይህ ሰነድ፣ በሜሪላንድ ክፍለ-ግዛት የትምህርት ክፍል የልዩ ትምህርት/የፈጥኖ ጣልቃ ገብነት አገልግሎት ቅርንጫፍ የስራ ውጤት ለመሆኑ ተገቢውን ዋጋ ይስጡ:: ✦ የአካል ጉድለት ያለባቸው አሜሪካዊያን ድንጋጌ(ADA)ን በሚመልከት ሲጠየቅ፣ ይህ ሰነድ በሌላ የተለየ አማራጭ አቀራረብ ተዘጋጅቶ ይገኛል:: የልዩ ትምህርት ክፍሉን በሚቀጥሉት አድራሻዎች ያነጋግሩ፣ 410-767-0261 በድምጽ፣ 410-333-2661 ፋክስ፣ 410-333-0731 TDD.



3/04




# ገለልተኛ የቅሬታ አፈታት ሂደት በፈጥኖ ጣልቃ ገብነት ሥርዓት


የሜሪላንድ ክፍለ-ግዛት የትምህርት ክፍል
የልዩ ትምህርት ቅርንጫፍ/የፈጥኖ ጣልቃ ገብነት አገልግሎት፣
የሜሪላንድ የለጋ ሕጻናትና ድክ-ድክ የሚሉ ልጆች ፕሮግራም


Amharic

አንዳንድ ጊዜ፤ ስለ አንዳንዶቹ የፈጥኖ ጣልቃ ገብነት ሥርዓት አካሄዶች ላይ የአገልግሎቱ አቅራቢዎችና ወላጆች የማይስማሙባቸው ሁኔታዎች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ እነዚህም ቀጥሎ ያሉትን ይጨምራሉ፤

- ባለመብትነትን ስለመወሰን
- አንድን ሕጻን ስለማመዛዘንና መገምገም
- መብቱ ላለው ልጅ የፈጥኖ ጣልቃ ገብነት አገልግሎትን ስለማቅረብ
- ለፈጥኖ ጣልቃ ገብነት አገልግሎት የወላጆች ገንዘባዊ ግዴታ

ይህ ሁኔታ ሲያጋጥም፤ መግባብት በጣም አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል፤ እናም ሁለቱ ወገኖችም በጋራ የሚያስማማቸው ውሳኔ ላይ ለመድረስ ይሳናቸዋል፡፡

አቤቱታቸውን (ቅሬታቸውን) ለማስተናገድ ለወላጆች ምቹ የሚሆነው አንዱ አማራጭም ሽምግልና—በአንድ ሽምጋይ (አደራዳሪ) ረዳትነት ሁለቱ ወገኖች በጋራ የሚስማሙበት ውሳኔ ላይ እንዲደርሱ የሚያስችላቸው ዓይነት በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የቅሬታ አፈታት ስልት ነው፡፡ ይህን አማራጭ ለሚመለከት የበለጠ ኢንፎርሜሽንም፤ ከሜሪላንድ የለጋ ሕጻናትና ድክ-ድክ የሚሉ ልጆች ፕሮግራም ማግኘት የሚቻለውን *ድርድር በፈጥኖ ጣልቃ ገብነት ሥርዓት የሚል ርዕስ ያለውን* ጽሁፍ ይመልከቱ፡፡

**ገለልተኛ የቅሬታ አፈታት ሂደት** ከሁለቱም ወገኖች የሚቀርቡ አቤቱታዎችን የሚያስተናግድ ሥርዓታዊ ሂደት ነው፡፡ ይህ ሂደት በሁለቱም ወገኖች በኩል የቀረቡ ማስረጃዎችን ካየና የቀረቡ ምስክሮችንም ካዳመጠ በኋላ በአስተዳደራዊ ህግ ዳኛው የሚተላለፍ ውሳኔ አሰጣጥን ይጠይቃል፡፡

ገላትኛ የቅሬታ አፈታት ሁኔታ በይደር ቀጠሮ ላይ ሲሆን፤ የአካባቢው ፕሮግራምና ወላጆች ካልተስማሙበት በስተቀር፤ የፈጥኖ ጣልቃ ገብነት አገልግሎቶቹ አይስተጓጎሉም፡፡ አቤቱታው የቀዳሚ አገልግሎት ጥያቄን ያካተተ ማመልከቻ ከሆነ፤ ሕጻኑ አከራካሪ ያልሆኑትን የነዚህን አገልግሎቶች ክፍሎች ማግኘት ይችላል፡፡

ጉዳዩ በሚሰማበት ወቅት፤ ወላጆች የሚከተሉት መብቶች ይኖሯቸዋል፡፡

- አማካሪዎችና ስለአፋጣኝ ጣልቃ ገብነት አገልግሎት እውቀትና ሥልጠና ያላቸው ግለሰቦች አብረዋቸው በመሆን ምክር እንዲለግሷቸው፡
- ማስረጃ የማቅረብና የመከራከር፤ መስቀለኛ ጥያቄ የማድረግ፤ እና ምስክሮችም እንዲቀርቡ የማስገደድ፡
- ጉዳዩ እንዲሰማ ቀጠሮ ከተያዘበት ቢያንስ ከአምስት ቀናት በፊት ለነርሱ ያልተገለጹላቸው ማስረጃዎች እንዳይቀርቡ የመከልከል (የማገድ)፡

ጉዳዩ ከታየ በኋላ፤ ወላጆች የሚከተሉትን የማግኘትና የማድረግ መብቶች አሏቸው፡

- ስለጉዳዩ መታየት የቀረበው ጥያቄ፤ ለሜሪላንድ የለጋ ሕጻናትና ድክ-ድክ ባይ ሕጻናት ፕሮግራም ከደረሰው ከ30 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ውሳኔውን በጽሁፍ የመቀበል መብት፡
- የተሰማውን ጉዳይ የሚመለከት የጽሁፍ ወይም በዔሌክትሮኒካዊ ዘዴ የተቀነባበረ ዝርዝር ሀተታ ከክፍያ ነጻ ማግኘት፡
- በውስኔው ያልተደሰቱ ሲሆን፤ ለክፍለ-ግዛቱ ወይም ለፌደራሉ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማለት፡

### ጉዳያቸው እንዲታይላቸው ለመጠየቅ፤ ወላጆች የሚከተሉትን ማሟላት ይጠበቅባቸዋል፤

*ገለልተኛ የቅሬታዎች አፈታት ሂደት ቅጽን መሙላት*፤ ቅጹም ከሜሪላንድ የለጋ ሕጻናትና ድክ-ድክ ባይ ሕጻናት ፕሮግራም፤ በሜሪላንድ ክፍለ-ግዛት የትምህርት ክፍል፤ የልዩ ትምህርት ቅርንጫፍ/የፈጥኖ ጣልቃ ገብነት አገልግሎት ይገኛል፡፡

በቅጹ ላይ፤ ከጉዳዩ መሰማት ቀደም ብሎ፤ ወላጆች በሽምግልና ድርድር ለመሳተፍ ይመርጡ እንደሆነ አማራጭ ሁኔታ ተሰጥቷቸዋል፡፡ ወላጆች ድርድርን መርጠው ሳለ ነገር ግን በድርድሩ ሂደት ሁለቱ ወገኖች በጋራ የሚስማሙበት ውሳኔ ላይ መድረስ ካቃታቸው፤ ወላጆች አሁንም ቢሆን *አቤቱታቸው በገለልተኛ የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት* እንዲታይላቸው የመጠየቅ መብት አላቸው፡፡